# ውዳሴ ግድብ እና በተፋሰሱ አገራት ያለው እድምታ

የውዳሴ ግድብ መሰረት መጣል የራሱ የታሪክ ሄድት አለው የት ቦታ እና ባጀት ማድረግ አይቻል እንጂ የአባይ ወንዝ ለልማት እንዲውል የሁሉ ኢትዮጵያን ወዳጆች ርእይ ነው። የእውነተኛ አገር ወዳድ ግለሰቦች ፣ ሙሁራን ፣ የውሃ ባለሙያተኞች፣ የውሃ ሃብት ሚኒስትሮች እና የአገሪቷ መሪዎች ተሳትፈዋል። ከናይል ተፋሰሱ አገሮች (Nile Basin) ጋር ለረጅም ዘመናት አብሮ መስራት እና ትብብሮሽ ሲያደርጉ ቆይተዋል። ኢትዮጵያ ለብሉ ናይል ወንዝ የምታበረክተው የአስተዋፅኦ መጠን እና ባለድርሻነት የናይል ተፋሰሱ ሃገራት እንዲረዱ አድርገዋል። ለዓለም ህዝብ እና መንግስታት የሃብቱ ከፍተኛ ባለ ድርሻ አገራችን ኢትዮጵያ እንደሆነች አሳይተዋል። በአባይ ወንዝ ላይ ስራዎችን ጠንክሮ በመስራት ሃገራችን የሃብቱ ተጠቃሚ እንድትሆን የኢኮኖሚ እና የሃድሮ ፖለቲካ ስራዎችን ሰርተዋል።በናይል ተፋሰስ ሃገራት (Nile Basin) በተደረጉ አስቸጋሪ ውይይቶች፣የጥናት ስራዎች እና ስብሰባዎች ተስትፈዋል የአገራችንንም የባለቤትነት ድርሻ አሳይተዋል።

የውዳሴው ግድብ እንዴት መሰረት ተጣለ፣ የግድቡ መሰረት ሲጣል ወደ ግንባታ የሚያስከሄዱ የጥናትና የግንባታው ቁጥጥር ስራዎች የተከናወኑት እንዴት ነበር።የቅድመ ጥናት እንዴት የውጪ አጥኚ ድርጅቶችን አላሳተፈም በውዳሴ ግድብ ዙርያ በኢትዮትያ በሱዳን እና በግብፅ አገራት መክከል እየተካሄደ ያለው ውዝግብ መንስሄው። የአስተሳሰብ ለውጥ በተፋሰሱ አገራት እንዴት ማምጣት ይቻላል የሚሉትን እንደ መሪ ሃሳብ በመውሰድ በዝርዝር እንመመልከት።

በአባይ ወንዝ የታቀዱ የሃይድሮ ፖወር ፕሮጀክቶች እና ውዳሴ ግድብ

በውሃ ሃብት ሚኒስቴር ከተዘጋጁት ሶስት የሀይድሮ ፖወር ፕሮጀክቶች በ 2003 ለውጪ አጥኚ ድርጅት እና በሃድሮ ፓወር ግንባታ ልምድ ላላቸው ድርጅቶች የተዘጋጀው ሰነድ ቀርቦ ነበር ።በጥናት ስራዎች ላይ ለመሳተፍ ፍቃደያ የነበሩ እንደነበረና ለግንባታ የሚውለውን ወጪ ከአለም አቀፍ አበዳሪዎች ማስገኘት በሚቻልበት ሁኔታ ንግግሮች እና መግባባቶች እንደነበሩ አስታውሳለሁ። በሚኒስቴሩ ውስጥ በሚሰሩ በለሙያተኞችም የውጪ አጥኝዎች እንዲሳተፉ የማድረግ ጥረቶች ተደርገው ነበር። ሆኖም ግን በቀጣይነት የጨረታ ሰነዶች ተዘጋጅተው ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል ከባለስልጣናት ምላሽ ባለመገኘቱ ንግግሮቹ ተፈፃሚ መሆን አልቻሉም። ቆይቶም ውዳሴ ተብሎ መሰረት በመጣል እና ያለ ብድር በራሳችን አቅም እንሰራለን የሚለው ሃሳብ መምጣቱ አዲስ ክስተት እና ያልተጠበቀ ነበር። የቀረቡትም ሶስት የሃይድሮ ፖወር ፕሮጀክቶች፣ አንዱ በኢትዮጵያ ሱዳን ድንበር አካባቢ (Mendaia Project) እና ሁለት ሊሎች ፕሮጀክቶች (Birbir and Karadobi Projects) ነበሩ።እንዲገነቡ የታቀዱት የሃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች በውሃ ሃብት ሚኒስቴር (MWR)ተመርጠው ለግንባታ ዝግጁ በማድረግ በኦገስት 2002 በቀረበው የፕሮጀት ፕሮፖዛል ዶክመንቶች ሲሆኑ ። በፕሮጀት ፕሮፖዛል ላይም እነዚህ የሃይድሮ ፖወር ፕሮጀክቶች ፕሮፖዛሎች (1) Eastern-Nile River Basin አገሮች The Eastern Nile Subsidiary Action Program (ENSAP) ተቀባይነት አግኝተው እንደነበር ያሳያል።

በ 2004 ላይ በአንድ በውጪ አጥኚ ድርጅት በኩል በኢትዮትያ ሱዳን ድንበር አካባቢ (የአሁኑ ውዳሴ ግድብ) ላይ ሳይሆን ከ ሶስቱ በአንዱ የጥናት ስራ እንደተካሄደ የሚያሳይ መረጃ ከኢንተርነት ላይ ማየት ይቻ|ላል(2 ) መረጃው ኖሮ በአሁኑ ሰአት መናገር ባይቻልም ይህንን ጥናት በጨረታ ተወዳድሮ ያሸነፈው ማን መሆኑን መረጋገጥ ይኖርበታል እላለሁ። 2018 ሜይ ላይ ደግሞ በግንባታ ላይ ለማሳተፍ Kardabi በሚለው ላይ መሳተፍ የሚያስችል ጨረታ ወጥቶ ተመልክቻለሁ ጥናቱ በማን ተተግብሮ ይሆን በምንስ መልክ የሚታይ ነው።(3)

የአሁኑ የውዳሴ ግድብ ጥናት በውጪ አጥኤዎች ተከናውኖ ግንባታ መካሄድ ይችል ነበር ወይ ለሚል ሃሳብ ዛሪ ላይ ሆነን ሳስበው ያስቸግር ነበር ፣ በቀደም ዘመናት በደርግ አገራችን በውሃ ሃብቶቿ ለመጠቀው የጀመረቻቸው ፕሮጀክቶች የመከኑ መሆን የቅርብ ግዜ ትዝታዎቻችን ናቸውና። የውዳሴ ግድብ ጥናት በውጪ አጥኤዎች ተከናውኖ ግንባታ መካሄድ ይችል ነበር ለሚለውን ሃሳብ ሁኔታዎች ስንመለከት በዋንኛነት ከአገራችን ወደታች የምትገኘው የውሃ ሃብቱ ተጠቃሚ አገር ግብፅ በተፈጠረባቸው የውስጥ ችግር አገራችንን የመተናኮል አቅማቸውን የተዳከመበት ስለነበር በአጥኚ ድርጅቶች ላይ የሚኖራቸው ጣልቃ ገብነት ትንሽ እድል የሰጠ

ነበር። ስለዚህም የግድቡ ባለርእይ የተባለላቸው አካላት ይህንን የተገነዘቡ ይመስላል በራሳችን አቅም፣ ያለውጪ አጥኚ ድርጅት ለመገንባት ሃሳብ ላይ የደረሱት።ከአገራችን የወደታች ያሉ የአባይ ወንዝ ተጠቃሚ አገራትም ፍላጎታቸውን እንደ ሚያሟላቸው በመገንዘባቸው በሚገነባውን የውዳሴ ግድብ ስምምነት እና መግባባት የደረሱት። እላይ በቀረበው ሰነድ በውዳሴው ባይሆን በድንበር ላይ ስለሚገነባ የሃድሮ ፓወር ግድብ ላይ የታች አገራት የተስማሙ እንደሆኑ ማየት ይቻላል። በተለይ ግብፅ በማንኛውም ልማት አይኞቿን ከማትነቅልባት አገራችን ላይ የዚህ ግድብ ግንባታ የበለጠ ተጠቃሚ እንደሚያደርጋት ግንዜቤ ስለነበራት ለግዜውም ችላ ብላ ነበር። በነዚህ ሁኔታዎች ትንፋሽ ያገኘችው አገራችን የውዳሴ ግድብን መሰረት ጥላ ግንባታው ውስጥ ገባች።

የውዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ግንባታ እና የአስተዳደር ስራዎች

በአንድ የግንባታ ፕሮጀክት ውስጥ በትንሹ የግባታው ባለቤት፣ ግንባታውን የሚያካሄድ ኮንትራክተር እና አማካሪ ድርጅቶች መኖር ይኖርባቸዋል። በተለይ አማካሪ ከጥናቱ ጀምሮ የፕርጀክቱን እድገት በጊዜው ሰሌዳው መሰረት የሚከታተል ፣ የግንባታ ባጀት በተገቢው ሁኔታ ግንባታውን ለሚያካሄደ አካል እንዲለቀቅለት የተሰሩትን ስራዎች ካረጋገጠ በሃላ የግባታው ባለቤት ክፍያዎችን እንዲፈፅም የሚጠይቅ አካል ነው። መረጃዎችንም ይሰበስባል፣ የተደረጉ የስብሰባ አጀንዳዎችን መግባባቶችን እና ውሳኔዎችም የሚያደራጅ እና የሚይዝ አካልም ሊኖር ግድ ይላል።ስለ አንድ ፕሮጀክት ግንባታ በተለይ ወደ ትልቁ ግድባችን ስንገባ ግን የየትኛው አማካሪ ድርጅት ስራውን ይከታተል ነበር የሚለው በግልፅ ማየት አይቻልም ። ሆኖም ግን የውዳሴውን ግድቡ ግንባታ የሚቆጣጠረው ድርጅት በግልፅ መታየት አለመቻሉ የለውም ለማለት አያስችልም፣ ምክንያቱም የንድፍ ስራ ሳይኖረው ግንባታው ስለማይጀመር። ግድቡ በሃሳብ ደረጀ አገሪቷን ለመጥቀም የተጀመረ እንደሆነ እስማማለሁ፣ ወደ ግንባታ የሚያስኬዱ የጥናት ስራዎች የዋጋ ተመን የተከናወኑት እንደነበር ግልፅ ነው። ለምን ታድያ የግንባታው ሄደት በየደረጃው ከወጣው ወጪ ላይ ተስማሚነት አልኖረውም፣የሁላችንም ጥያቄ ነው ለምዝበራውም መንገድ የከፈተ አሉታዊ እና ወሳኝ ነጥብ ምላሽ የሚያስፈልገው ነው። በቀረቡ የክፍያ ሰነዶች ላይ መታየት ይችላሉ የፕሮጀክቱ ተቆጣጣሪ እና ስራ አስኪያጅ ሙያዊ ተግባራቸው ያልገበሩ መሆኑን ያሳያል።

በውዳሴ ግድብ ዙርያ ለምን ንትርኮች ከኢትይጵያ ወደ ታች ባሉት የተፋሰሱ አገሮች ተከሰተ

በሁሉም ናይል ተፋሰስ (Nile Basin) ተጠቃሚ አገሮች የተደረሱ መግባባቶች ለአሁኑ የምስራቃዊ አባይ ተፋሰስ (Eastern-Nile River Basin ) አገራት ለፈጠሩት ንትርክ ድባብ የፈጠረ ይመስለኛል ። በአብዛኛው በአባይ ተፋሰስ አገራት ስምምነት እና ተቀባይነት ያገኘው ሃሳብ፣ አገራት ፍትሃዊና እኩለታዊ የሆነ የወንዙ አጠቃቀም መብት አላቸው የሚለውን መሰረት ያደረገ ነበር። በትክክል ሃብቱን እንዴት መከፋፈል እንዲሚቻል ውሳኔ ላይ ተደርሶ ተግባራዊ ባይደረግም፣ ፍትሃዊ አጠቃቀም የሚለው ሃሳብ የጋራው ዓላማ ላይ የተቀመጠ እና ተቀባይነትን ያገኘ ይመስላል። በምስራቃዊ አባይ ተፋሰስ (Eastern-Nile River Basin ) ውስጥ ግን መሰረት ጥሎ የነበረው ሃሳብ፣ የሚገኘውን ጥቅም እንካፈለው የሚልውን ነው ስምምነት ላይ አልተደረሰሰበትም። የሚገኘውን ጥቅም እንካፈለው የሚለው ከኢትዮጵያ ወደታች ባሉ አገራት የሚቀርበው ሃሳብ ቀደም ብሎ ከአባይ ወንዝ የሚሄደውን የፍሰት መጠን ባልቀነሰ መጠን ሙሉ በሙሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያግዝ እና ገደብ በሌለውን አጠቃቀም በተለይ የታች አገራት ፍላጎቶች ለሚሟላት ያለመ ነው። ዓላማውም አገራቱ ከዚህ ቀደም ይዘው የነበሩትን ፍላጎቶችን እውቅናን ለመግኘት መሰረት ያደረጉ ድብቅ ሃሳብን የሚያስተገብር ነበር። የውዳሴ ግድብ የግንባታው መሰረት ሲጣል በግድቡ ዙርያ የሚፈጠረው ሁኔታ እነዚህ የታች ተጠቃሚ አገሮች አያውቁትም ነበር ማለት አይቻልም የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ተስማምተውበት ነበርና ። የግድቡን የውሃ የመያዝ አቅም የወደታች አገራት ያውቁት ነበር የሚያሰኝ ሃሳብ ነው የሚሰጠን ። ከውዳሴው ግድቡ የሚገኘው የኢትዮጵያ ጥቅም የሃድሮ ፓወር ለምሳሌ ብንወስድ የሃይል ሽያጭ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ሙሉ በሙሉ የወንዙን የውሃ ፍሰት የማይነካ ነው። አመቱን በሙሉ ከሃይል ማመንጫው የተስተካከለ ፍሰት ለታች አገራት መስጠት ይችላል። እየተገነባ ባለው ግድብ ላይ በተለያየ ግዜ የመነታርኪያ ሃሳቦችን እያመጡ ግድቡ እንዲቆም ወይም ከፍታው እንዲቀስ የሚሰነዝሯቸው ሃሳቦች በአባይ ተፋሰስ ላይ ሊሎች ልማቶች አገራችን እንደምታከናውን በማስብ ነው። ችግሮችን በሚገነባው ግድቡ ዙርያ እንዳሉ የሚነግሩን ለማዘናጊያነት የሚጠቀሙበት ዘዴ ሲሆን፣ በአጠቃላይ በአባይ ተፋሰስ አገራት ስምምነት የተደረሰበትን ሃሳብ ተግባራዊ እንዳይሆን በመከላከያነት የሚጠቀሙበት እስትራቴጅ ነው። ግድቡም አልቆ የውሃ የመያዝ አቅም እና ከፍታ ሲረጋገጥ ለታቀደለት አላማ በተገቢው ሁኔታ መዋል ያስችላል፣ መጠናቸው የሚታወቅ ፍሰት በመለኪያ መስፈርቶች ተቀምረው አገልግሎት ላይ

ስለሚውሉ አሉታዊ እድገትን ለአገራችን ያመጣል። የፍሰት መጠንንም መሰረት የሚያደርገው ስምምነቶች ስለሚኖር ለንትርኮች መፍትሄ ይሆናል።

የአስተሳሰብ ለውጥ በተፋሰሱ አገራት እንዴት ማምጣት ይቻላል

በኢትዮጵያ ውስጥ ግድቦች ቢገነቡ ከወደታች አገሮች አገራችን የተሻል የአየር ጠባይ ስለአላት በትነት የሚባክኑ የተፋሰሱን የውሃ ሃብት መጠበቅ ይቻላል ። በህዝባችን እና በአካባቢ ላይ የሚያስከትለው ችግሮች በአካባቢ ጥናት ግምገማ ላይ ግድቡ ከሚሰጠው ጥቅም አንፃር በማወዳደር መታየት ይገባዋል።በአባይ ወንዝ ላይ የውዳሴ ግድብ የምታካሄደው አገራችን ከግንባታው ጎን ለጎን የሃይል ማመንጨት ስራዎችን ማካሄድ ያስፈልጋታል። ግድቡ መሙላት እና በሙሉ አቅም ለታቀደለት የሃይል ማመንጫነት ለማድረስ ወሳኝነት የሚኖረው ሁሉም የታች ተጠቃሚ አገራት በጎ አሳቢነት ሲኖራቸው ነው።

በውዳሴም ግድብ የውሃ የመያዝ አቅም ላይ እየተነሱ ያሉ ውዝግቦች መሰረታቸው ሃብቱን አትንኩብኝ ከማለት ውጪ ከግድቡ ከፍታ ጋር ቀጥታና ተያያዥነት ያለቸው መሆን የለባቸውም። ግድቡ ቢፈርስ የሚለውን ሃሳብ ለመመለስ የውዳሴ ግድብ ግንባታ መሰረት ያደረገው በኮንክሪት እና በብረት (RCC & Rock fill Dam) የግንባት ቴክኖሎጂ ላይ በመሆኑ ስጋቱ በጣም የቀነሰ ነው። ለማወዳደርያነትም በአባይ ወንዝ ላይ ግብፅ የገነባቸው የአስዋን ግድብ ሮክ ፊልድ ዳም ሲሆን፣ ከፍተኛ የሆነ የመፍረስ አደጋ ሊያጋጥመው እንደሚችል ጥናቶች ያሳያሉ። ወደ ታች ያሉ አገራት የሚሄደው የወንዙ ውሃ ጥራት ላይ የሚፈጠር ተጽእኖ ሱዳን ላይ ብቻ እንዲጠና የተቀመጠለት በመሆኑ ከተጨማሪ ውዝግቦች እና ግዜን ከማባከን አድኖል። ስለዚህም ማለት አያስፈልግም ስምምነቶች አንድ መራፍ ሄዳዋልና።ግንባታው ካለቀም በሃላ ውዝግቦች ወደፊት አይከሰቱም ማለት አያቻልም ሆኖም ግን ወደታች ያሉት አገራት በአሉታዊነት አስተሳሰብ፣ በአዳዲስ መርሆዎች በልፅገው ፣ ራዕይያቸውን ከልሰው ፣ እኛ ብቻ የሚለውን የአመታት አትንኩብን ባይነት መርህ ትትው ከንትርክ ይልቅ ስምምነት የተማሩ መሆን ይገባቸዋል ።

በአጭሩ የተፋሰሱን የውሃ ሃብት በአግባብ ለመጠቀም አማራጭ የሚሆነው ግን ውዳሴን የሚያክል ትልልቅ ግድቦች በኢትዮጵያ ምድር መገንባት ነው እላለሁ። አዳዲስ ግድቦችንም ለአገልግሎት ስናበቃ መሰረታዊ የልማት ስራትን ስለምንከተል የወንዙን ሃብት ቆጥቦ ለተፋሰሱ አገራት ተጠቃሚነትን ማሳደግ ያስችላል፣ የሚፈጠሩ ችግሮችን ማስወገድ እንችላለን። ትልቁ እና ዋናው ነገር ወንዙ ያለውን እምቅ ሃበት አገራችንን ባለቤት በማድረግ ከአምላክ በተሰጠን ገፀ በረከት ህዝባችንን ከርሃብ፣ ከድህነት አላቀን በስምምነት በሃብቱ የመጠቀምን ሃይል እና እምነት በውስጣችን ማኖር ነው። ብዙ ስራዎች ከግድቡ በታች ባሉ አገራት ተሰርተዋል፣ አገራችን ተጠቃሚ አትሁን የሚል ስራት ይኑር የሚለን አካል መኖር የለበትም።ሃብቱ በተገቢው ተጠንቶ በቁጠባ በመተሳሰብ እና በእኩልነት መንፈስ ለአገልግሎት ቢውል፣ ለሁሉም ተጠቃሚ ሃገራት በቂ ማድረግ የማይቻልበት ሁኔታ የለም።

በቀለ
twldbekele@gmail.com

(1) THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA. MINISTRY OF WATER RESOURCES MENDALA HYDROPOWER DEVELOPMENT PROJECT. PROJECT PROPOSAL AUGUST.2002 A,A
(2) http://www.norwayexports.no/sectors/news/feasibility-study-of-baro- and-pre-feasibility-study-of-karadobi-hydropower-projects-ethiopia/
(3) https://www.esi-africa.com/ethiopian-electric-power-invites-bidders-to-operate-bot-project/